በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 1.0/566/08
Ref. No. 22 ግንቦት 2008
ቀን
Date

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡ የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፤

የዕቃ ፍተሻ እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ ሥርዓት የሚፈፀምባቸውን እቃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 119/2008 ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የላክንላችሁ ስለሆነ መመሪያው ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አብርሃም ንጉሴ
ቲ/ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፤

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሕግ ማስከበር ስራዎች ዘርፍ
- አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም፣ ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ፕሮግራም፣ ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ስራዎች ዘርፍ
- ለአዲስ አበባ ታክስ ፕሮግራም፣ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለህግ ጥናት፣ ረቂቅና ዝግጅት ስልጠና ዳይሬክቶሬት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ/ Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ዳይሬክቶሬት

- ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለየታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለወንጀል ምርመራ ዳይሬክቶሬት
- ለዐቃቤ ሕግ ቢሮ
- ለአ.አ. ወንጀልና ፍትሐብሄር ጉዳዮች ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለፌዴራል ወንጀልና ፍትሐብሄር ጉዳዮች ክትትል ዳይሬክቶት
- ለህግ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት
- ለህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለድንበር አስተዳደርና ኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለዕቅድና አፈጻጸም ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለየተያዙና የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጥናትና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለአገር ውስጥ ታክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ኦዲት አሰራር ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለለውጥ ትግበራ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለክልሎች ድጋፍና ትብብር ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለሴቶች ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት
- ለትምህርትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትጌሽን ኦዲት የስራ ሂደት
- ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ፕሮግራም ልማት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት
- ለሀብት አስተዳደር ቢሮ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ቅ/ጽ/ቤቶች

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አዲስ አበባ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመርካቶ ቁጥር 1 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- መርካቶ ቁጥር 2 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቁጥር 1 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቁጥር 2 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአራዳ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለየካ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለልደታ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- አዲስ ከተማ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

- ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት /አዳማ/
- ለሞጆ ቅ/ጽ/ቤት /ሞጆ/
- ለባህርዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ባህርዳር/
- ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /መቀሌ/
- ለድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ድሬደዋ/
- ለሚሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ሚሌ/
- ለጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ጅግጅጋ/
- ለሞያሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ሞያሌ/
- ለጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ጅማ/
- ለጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት /ጋላፊ/
- ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት /ኮምቦልቻ/
- ሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት /ሐዋሳ/

# የዕቃ ፍተሻ እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ ሥርዓት የሚፈፀምባቸውን እቃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 119/2008

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ግንቦት 2008 ዓ.ም

# የዕቃ ፍተሻ እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ ሥርዓት የሚፈፀምባቸውን እቃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 119/2008

የሀገሪቱ የወጪና ገቢ ዕቃዎች እንቅስቃሴ እያደገ የመጣ በመሆኑ እና ወደፊትም በዚሁ ፍጥነት ዕድገቱ እንደሚቀጥል ግምት በመውሰድ ከዕድገቱ ጋር የተጣጣመ ዘመናዊ የዕቃ ፍተሻ አሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ቀረጥና ታክስ በአግባቡ መሰብሰብና የጉምሩክ ወንጀሎችን መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ በሚደረግ ፍተሻና ቁጥጥር ምክንያት የሚባክነውን ጊዜ፣ በዕቃዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማስቀረትና ቁጥጥሩን በአስተማማኝ ሁኔታ ማከናወን የሚያስችል በመሳሪያ የሚታገዝ ፍተሻ በማከናወን በሰው የሚደረግ አካላዊ ፍተሻን መጠን መቀነስና መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

በጉምሩክ ትራንዚት ሂደት ላይ ያሉና ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ እቃዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚፈጸምባቸውን እቃዎች ዓይነት ለመዘርዘርና ከጉምሩክ ቁጥጥር የሚለቀቁበትን ሥርዓት በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፣

እቃዎችን በጉምሩክ ትራንዚት ጉዞ ወቅትና ከጉምሩክ ቁጥጥር ለነጻ ዝውውር ከመልቀቅ አሰራር ጋር ተያይዞ ሊፈጠር የሚችለውን ተገቢ ያልሆነ የአገልግሎት መጓተት ለማስተካከል ፈጣንና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 23/8 እና አንቀጽ 180(1) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የዕቃ ፍተሻ እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈፀምባቸውን እቃዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 119/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡



2. <u>ትርጉም</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) “ቅድሚያ ተሰጥቶት የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምበት እቃ” ማለት በቀላሉ የሚቀጣጠል፣ የሚተን፣ የሚበላሽ፣ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በአስቸኳይ የሚፈለግ እና/ ወይም ያለው የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ከፍተኛ ሲሆን እንዲሁም በመጋዘን ውስጥ በመቆየት በንብረት ወይም በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ማንኛውንም እቃ ይጨምራል፡፡
2) “የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ” ማለት በገቢና ወጪ ዕቃ ላይ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈፀምበት ወይም/እና ታክስ የሚሰበሰብበት በባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ስር የሚተዳደር ጣቢያ ነው፡፡
3) “ቅርንጫፍ ጽ/ቤት” ማለት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ስር የተቋቋሙ የጉምሩክ ስነ ስርዓት የሚፈጸምባቸው ጽህፈት ቤቶች ናቸው፡፡
4) “ስታንዳርድ ዝርዝር የዕቃ መግለጫ” ማለት በዲክላራሲዮን ላይ ስለተመዘገቡት ዕቃዎች ዝርዝር ያስተሻሽግ ሁኔታ፣ የዕቃዎች ብዛት፣ የተሰሩበትን ማቴሪያል፣ የዕቃውን ዓይነት፣ የተመረቱበትን ሀገር፣ ወዘተ በየዕቃው ዓይነት በመለየት የሚገልፅ ሰነድ ነው፡፡
5) “ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ ወይም ሰማያዊ የሥጋት ደረጃ” ማለት እንደቅደም ተከተሉ ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና እጅግ ዝቅተኛ የሥጋት ደረጃ ተብለው በተለዋጭ የሚገለፁት ናቸው፡፡
6) ”ተሽከርካሪ ” ማለት በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስ ዕቃ ሲሆን በሞተር የሚንቀሳቀሱ ባለሁለት እግሮችን አይጨምርም፡፡
7) ”የውጭ ፍተሻ” ማለት ከቅ/ጽ/ቤቶች ወይም ጣቢያዎች ውጭ ባለስልጣኑ በፈቀደው ቦታ የሚከናወን ፍተሻ ሲሆን ዲክላራሲዮኑ ከተከፈተበት ቅ/ጽ/ቤት ውጭ በሌላ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ የሚደረግ ፍተሻን ይጨምራል፡፡
8) “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶችን ወይም ጣቢያዎችን ይጨምራል፤
9) “አዋጅ” ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው፡፡
10) ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

1) ወደ አገር በሚገቡ፣ በተላላፊ ወይም ከአገር በሚወጡ ዕቃዎች ላይ ለሚደረግ ፍተሻ እና
2) ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት በሚፈጸምባቸው ዕቃዎች እና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

## ክፍል ሁለት

## በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ስለመፈተሽ

4. መርህ

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ከተዘረዘሩት ዕቃዎች ውጪ ያሉ ማናቸውም ገቢና ወጪ ዕቃዎች የሥጋት ደረጃቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ይፈተሻሉ፡፡

5. በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ፍተሻ የማይደረግባቸው ዕቃዎች

የሚከተሉት ዕቃዎች በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ፍተሻ አይደረግባቸውም፤

ሀ/ ማናቸውም በህይወት ያሉ እንስሳት፤

ለ/ የዲፕሎማቶች ዕቃዎች፣

ሐ/ ከመፈተሻ መሳሪያ ጋር በሚፈጠረው ግንኙነት የመቀጣጠልና የመፈንዳት ባህሪ ስላላቸው አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ዕቃዎች፣

መ/ የስጋት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ዕቃዎችና

ሠ/ ለሀገር መከላከያ እና/ወይም ለመረጃ ደህንነት አገልግሎት ወደ ሀገር የሚገቡና ለጥገና ከሀገር የሚወጡ እቃዎች፤

ሠ/ ሌሎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው ሰርኩላር ከፍተሻ ነፃ የሚደረጉ ዕቃዎች

6. የመፈተሻ ቦታ /ጣቢያ/

1) የዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ማናቸውም ዕቃዎች በጉምሩክ መውጫና መግቢያ በሮች፣ በተፈቀዱ የጉምሩክ መጋዘኖች እንዲሁም በመተላለፊያ መንገዶች ላይ ባሉ የዕቃ መፈተሻ መሳሪያዎች በሚገኙበት ሥፍራ ይፈተሻሉ፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ጊዜ ፍተሻ የተደረገበት ዕቃ አስገዳጅ ወይም አስፈላጊ ሁኔታ አለ ካልተባለ በስተቀር በድጋሚ በሌላ ጣቢያ በመሳሪያ ፍተሻ አይደረግበትም፡፡

7. በፍተሻ ወቅት ስለሚገኝ ልዩነት

1) በመሳሪያ በተደረገ ፍተሻ የተገኘው ዕቃ ክልክላ የተደረገበት ከሆነ ወይም የቀረጥና ታክስ መጠኑ ከ10 በመቶ በላይ ልዩነት የተገኘባቸውን ዕቃዎች በተመለከተ ልዩነቱን ያገኘው ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ የፍተሻ ውጤቱን ከዝርዝር መግለጫ ጋር ዕቃውን አሳጅቦ ዲክላራሲዮን ለተከፈተበት ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ያስተላልፋል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገኘው ልዩነት ከ10 በመቶ በታች ከሆነ ዕቃውን በሲል በማሸግ ሳይታጀብ በመንገድ ወረቀቱ ላይ ስለልዩነቱ ማስታወሻ በመጻፍ ለተከፈተበት ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ያስተላልፋል፡፡

3) ዲክላራሲዮን የተከፈተበት ጣቢያም የተላለፈለትን የፍተሻ ውጤትና መግለጫ መሠረት በማድረግ ዕቃው ሙሉ በሙሉ እንዲፈተሽ በማድረግ የተባለው ልዩነት መኖሩን ካረጋገጠ በጉዳዩ ላይ እንደሁኔታው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲታይ ወይም በወንጀል ምርመራ እንዲጣራና በፍ/ቤት ተገቢው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡ የደረሰበትንም የፍተሻ ውጤት አሳጅቦ ለላከው ቅ/ጽ/ቤት ውጤቱን ባወቀ 10/አስር/ የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

4) ወጪ ዕቃን በተመለከተ በመሳርያ በተደረገ ፍተሻ ልዩነት የተገኘ እንደሆነ ፍተሻውን ያደረገው ጣቢያ ልዩነቱን በመመዝገብ ዕቃዎቹ ከሃገር እንዲወጡ ያደርጋል፣ ልዩነቱንም ዲክላራሲዮን ለተሞላበት ጣቢያ ወዲያውኑ ያስተላልፋል፣ የተላለፈለት ጣቢያም እንደሁኔታው በልዩነቱ ላይ በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲታይ ወይም በወንጀል ምርመራ እንዲጣራና በፍ/ቤት ተገቢው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

5) በመሳሪያ የተደረገ ፍተሻ ልዩነት መኖሩ በቀጣይ በአካል በተደገረ ፍተሻ ልዩነት ያልተገኘበት ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ሆን ተብሎ ያለአግባብ የተሰጠ የሀሰት ማስረጃ የተገኘ እንደሆነ ማስረጃ የሰጠው ኦፊሰር ወይም ኃላፊ በሠራተኛ መተዳደሪያ ደንቡ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ህግ መሠረት ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ አካላዊ የዕቃ ፍተሻ

8. መርህ

በዚህ መመሪያ መሠረት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው፣ ጥቆማ ወይም መረጃ የቀረበባቸው እና ማናቸውም ገቢና ወጪ ዕቃዎች የሥጋት ሥራ አመራርን መሠረት በማድረግ አካላዊ የዕቃ ፍተሻ ይደረግባቸዋል፡፡

9. በናሙና ስለሚፈተሹ ዕቃዎች

1) በሥጋት ሥራ አመራር የሥጋት ደረጃቸው ቀይ የሆኑ ወይም የሥጋት ደረጃቸው ቢጫ ሆነው ወደ ቀይ የተለወጡ ወይም የሥጋት ደረጃቸው አረንጓዴ ሆነው ወደ ቀይ የተለወጡ ወይም የሥጋት ደረጃቸው ሰማያዊ ሆነው ወደ ቀይ የተለወጡ ዕቃዎች ስታንዳርድ ዝርዝር የዕቃ መግለጫ ሰነድ ከቀረበላቸው ዕቃዎች በዓይነታቸው ተለይተው ከተደረደሩ በኋላ ከተመሳሳይ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

የዕቃዎች ጥቅል ላይ አጠቃላይ ጭነቱን እንዲወክል በማድረግ በሚከተለው ሁኔታና ስኬል መሠረት ናሙና እየተወሰደ ፍተሻው ይከናወናል፡፡

ሀ/ ከ1 እስከ 20 ጥቅል ከሆኑት፣ 4 ጥቅል ናሙናዎችን፤

ለ/ ከ21 እስከ 40 ጥቅል ከሆኑት፣ 8 ጥቅል ናሙናዎችን

ሐ/ ከ41 አስከ 60 ጥቅል ከሆኑት፣12 ጥቅል ናሙናዎችን፤

መ/ ከ61 እስከ 80 ጥቅል ከሆኑት፣16 ጥቅል ናሙናዎችን

ሠ/ ከ81 እስከ 100 ጥቅል ከሆኑት፣ 20 ጥቅል ናሙናዎችን፤

ረ/ ከ100 ጥቅል በላይ ከሆነ በእያንዳንዱ ተጨማሪ መቶ ጥቅል ላይ 20 ጥቅል ናሙናዎችን በመውሰድ ፍተሻ ይከናወናል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተደነገገው ቢኖርም የሚፈተሸው ዕቃ ብረት በሚሆንበት ጊዜ የዕቃው ባለቤት እቃዎቹን የሚዛን ወረቀት እንዲያመጣ በማድረግ ልዩነት ያለው መሆኑ ይታያል፡፡ የሚፈተሸው እቃ ተሽከርካሪ በሚሆንበት ጊዜ ፍተሻው የሚደረገው ሙሉ በሙሉ ይሆናል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተደነገገው ቢኖርም በመጀመሪያ ከተወሰዱት ናሙናዎች በተደረገ ፍተሻ ልዩነት ከተገኘ ወይም ለዕቃዎቹ የቀረበው ስታንዳርድ ዝርዝር የዕቃ መግለጫ ሰነድ መሠረት ካልሆነ በዲክላራሲዮኑ በተመዘገቡት ዕቃዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ፍተሻ ይከናወናል፡፡ ሆኖም በናሙና ፍተሻ የተገኘው አነስተኛ ነው ተብሎ በጉምሩክ ስነ- ስርዓት ሥራ ሂደት መሪው ሲታመን ልዩነቱን ለማረጋገጥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት በተመሳሳይ ናሙና በመውሰድ ፍተሻ ማድረግ ይቻላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት ናሙና ሲወሰድ የተፈተሹ ዕቃዎችን ካልተፈተሹት ለመለየት እንዲቻል የሚመለከተው ሃላፊ ወይም የፍተሻ ኦፊሰር ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ምልክት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5) የናሙና አወሳሰድ በኮምፒውተር ሲስተም አማካኝነት ተፈፃሚ እንዲሆን ባለስልጣኑ የሚዘረጋው አሰራር ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

10. <u>ድንገተኛ ፍተሻ</u>

1) ባለሥልጣኑ ጥቆማ ወይም መረጃ በደረሰው ጊዜ ወዲያውኑ ወደ ሀገር በሚገቡ፣ ከሀገር በሚወጡ ወይም በተላላፊ ዕቃዎች ላይ በሥራ ላይ ባለው የሥጋት ሥራ አመራር መርህ እና በተጨባጭ መረጃ ላይ በመመስረት ከሚያደርገው መደበኛ ፍተሻ ውጪ ዕቃዎችን በድንገት ሊፈትሽ ይችላል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚደረገው ድንገተኛ ፍተሻ የሥጋት ደረጃቸው ዝቅተኛ ወይም መካከለኛ በሆኑ ዕቃዎች እንዲሁም ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግው ድንገተኛ ፍተሻ በመደበኛ ፍተሻ የተወሰዱ ናሙናዎች ላይ ሙሉ በሙሉ በድጋሚ እና በተቀሩት ዕቃዎች ላይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በሚወሰድ ናሙና ይሆናል፡፡

4) ድንገተኛ ፍተሻ ተደርጎ ልዩነት የተኘበት እቃ ከአንድ ጣቢያ ወደ ሌላ ጣቢያ በመጓጓዝ ላይ ያለ ከሆነ ድንገተኛ ፍተሻ ያደረገው ጣቢያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7(1) እና (2) በተደነገገዉ መሰረት ይፈፅማል፡፡

5) በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚደረግ ድንገተኛ ፍተሻ አስቀድሞ በተደረገ ዝግጅት ወይም ዕቅድ መሰረት ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡

6) በዚህ መመሪያ መሰረት የተደረጉ ፍተሻዎች ሁሉ ላይ ድንገተኛ ፍተሻ ሊደረግ ይችላል፡፡

7) በተደረገው ድንገተኛ ፍተሻ ልዩነት የተገኘ እንደሆነ እና አስቀድሞ በተደረገው ፍተሻ ይኸው ልዩነት ያልተገለፀ እንደሆነ አስቀድሞ ፍተሻውን ያከናወነው ወይም ያከናወኑት ኦፊሰሮች በአዋጁና በሠራተኛ መተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

8) በድጋሚ በሚደረግ ፍተሻ የሚገኝ ልዩነት አስቀድሞ በአግባቡ በተወሰደ ናሙና ላይ ሳይሆን በናሙና ባልተወሰዱ ዕቃዎች ላይ የሚገኝ ልዩነት ከሆነ ፍተሻውን ባከናወነው ወይም ባከናወኑት ሠራተኞች ላይ ተጠያቂነት አያስከትልም፡፡

## ክፍል አራት

## የውጭ ፍተሻ

### 11. የውጭ ፍተሻ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የውጭ ፍተሻ እንዲፈቀድለት የሚጠይቅ ሰው ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀዉ የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት እና አስፈላጊ ሰነዶችን በማያያዝ ዲክለራሲዮን ለተከፈተበት ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2) የውጭ ፍተሻ ፈቃድ የሚሰጠው ዲክላራሲዮን በተከፈተበት የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ሲሆን፤

ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12 መሠረት የሚጠየቅ የውጭ ፍተሻን ገቢ ወይም ወጪ ዕቃ ቡድን አስተባባሪ ወይም እሱ በሚወክለው ሰው የውጭ ፍተሻ ፍቃድ ይሰጣል፡፡ ፍተሸዉን የፈቀደዉ የስራ ክፍል ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት በግልባጭ ማሳዎቅ ይኖርበታል፡፡

ለ/ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12 ከተዘረዘሩት ድርጅቶችና ዕቃዎች በተጨማሪ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ልዩ እና አሳማኝ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ ለቅ/ጽ/ቤቱ የጉምሩክ

ጉዳዮች ም/ሥራ አስኪያጅ የውጭ ፍተሻ ጥያቄ ሊቀርብና ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት የተፈቀደ የውጭ ፍተሻን በተመለከተ መረጃዎቹ ተለይተው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

12. <u>የውጭ ፍተሻ የሚፈቀድላቸው ድርጅቶች እና ዕቃዎች</u>

1) በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተዘረዘሩት ድርጅቶች እና ግለሰቦች ለሚያስመጧቸው ወይም የሚልኳቸው ማናቸውም ዕቃዎች በሚያቀርቡት ማመልከቻ መሰረት ከባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ውጭ ፍተሻ እንዲደረግ ይፈቀድላቸዋል ፤

ሀ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፤

ለ/ የወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ ግለሰቦችና ድርጅቶች፤

ሐ/ ክልላዊ እና አገራዊ የሆኑ የመንግስት የፕሮጀክቶች፤

መ/ የህዝብ ወይም የክልል የልማት ማህበራት፤

ሠ/ በተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽ ፕሮግራም የታቀፉ የመብት ተጠቃሚዎች

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተዘረዘሩት ውጪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች የሚያስመጣ ወይም የሚልክ ሰው በሚያቀርበው ማመልከቻ መሰረት ከባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ የውጭ ፍተሻ ሊፈቀድለት ይችላል ፣

ሀ/ የፋብሪካ ጥሬ ዕቃዎችና ኬሚካሎች እንዲሁም የተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸው ዕቃዎች፤

ለ/ ነዳጅ እና የነዳጅ ውጤቶች፤

ሐ/ በቅ/ጽ/ቤቱ ወይም ጣቢያው ውስጥ ለመፈተሽ አመቺ ያልሆኑ ትልልቅ የፋብሪካ ማሽነሪዎች፤

መ/ በአንድ አስመጪ በአንድ ጊዜ የሚመጡ እና ቁጥራቸው 20 እና ከ20 በላይ የሆኑ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ቁጥራቸው 40 የሆኑ ባጃጆች ፤

ሠ/ ማዳበሪያ፣የእርዳታ እህል እና ሌሎች ከዚሁ ጋር በተያያዘ በብዛት መጥተው ወደብ ላይ የሚታሸጉና ወደ ሀገር የሚጓጓዙ መሰል ዕቃዎች፣

ረ/ ወጪ ዕቃዎች፤

ሰ/ መኪና እና የህንጻ መስታወቶች፣

ሸ/ በቅ/ጽ/ቤቱ ወይም ጣቢያው ውስጥ ለመፈተሽ አመቺ ያልሆኑ የኢንቨስትመንት ዕቃዎች፤

ቀ/ በቅ/ጽ/ቤቱ ወይም ጣቢያው ውስጥ ለመፈተሽ ለማራገፍና ለመጫን አመቺ ያልሆኑ ዕቃዎች፤

3) በዚህ አንቀፅ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይነት ወይም ተወዳዳሪነት ላላቸው ዕቃዎችና ድርጅቶች የቅ/ጽ/ቤቱ የጉምሩክ ጉዳዮች ም/ሥራ አስኪያጅ የውጭ ፍተሻ ሊፈቅድ ይችላል፡፡



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

የውጭ ፍተሻ ስለሚደረግባቸው ቦታዎች

1) የፍተሻ ፈቃድ የሚሰጠው ቅ/ጽ/ቤት ወደ አገር በሚገቡ ወይም ከአገር በሚወጡ ዕቃዎች ዲክላራሲዮን ከቀረበበት የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅ/ጽ/ቤት ውጭ በሚገኙ የጉምሩክ ጣቢያዎች ወይም ቅ/ጽ/ቤቶች ፣ በመንግስት መ/ቤት እና ድርጅቶች ቅጥር ጊቢ፣ በመጋዘኖች፣ በፕሮጀክት ሳይቶች ፤ የኢንዱስትሪ ዞኖች የውጭ ፍተሻ እንዲደረግ ሊፈቀድ ይችላል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ ሌሎች ቦታዎች ላይ የውጪ ፍተሻ እንዲደረግ ለቅ/ጽ/ቤቱ የጉምሩክ ጉዳዮች ም/ሥራ አስኪያጅ ጥያቄ ሊቀርብና ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

14. የውጭ ፍተሻ የሚያደርግ ጣቢያ ወይም ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊነት

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የውጭ ፍተሻ የሚያደርግ የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅ/ጽ/ቤት የፍተሻውን ውጤት ለፈቀደው ቅ/ጽ/ቤት ፍተሻው በተጠናቀቀ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በፋክስ፣ በኢሜይል ወይም በአውትሉክ ማሳወቅ አለበት፤

2) የውጪ ፍተሻ የሚያደርግ ጣቢያ ወይም ቅ/ጽ/ቤት ኦሪጅናል የፍተሻ ውጤቱን በፋክስ፣ በኢሜይል ወይም በአውትሉክ ባሳወቀበት ዕለት በፓስታ ቤት በኩል ለፈቀደው የቅ/ጽ/ቤት መላክ ይኖርበታል።

3) የውጭ ፍተሻ የፈቀደው ቅ/ጽ/ቤትም በደረሰው ሪፓርት መሠረት አስፈላጊው ሥርዓት መፈፀሙን በማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ ዲክላራሲዮን መዝጋትን ጨምሮ ቀሪ ስራዎቹን ያከናወናል።

4) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7(4) ወይም አንቀፅ 10(5) መሠረት የተፈፀመ ጥፋትና የተወሰደ እርምጃ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለዋና መ/ቤቱ በሪፓርት መገለፅ አለበት።

5) የውጭ ፍተሻ ያከናወነ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ሀላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ካለከ የዲሲፕሊን ጥፋት እንደፈጸመ ተቆጥሮ በሰራተኛ አስተዳደር ደንብ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

15. የውጭ ፍተሻ አፈፃፀምና ዲክላራሲዮን የተከፈተበት ጣቢያ ኃላፊነት

1) በውጭ የሚደረግ ፍተሻ የስጋት ስራ አመራር ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ በዚህ መመሪያ ክፍል ሶስት በተመለከተው ሥርዓት መሠረት የአካል ፍተሻ ይፈፀማል።

2) የውጪ ፍተሻ ተደርጎ ልዩነት በተገኘ ጊዜ ልዩነቱ በጋራ ቁልፍ ታሽጎ በመፈራረም ይያዛል ወይም ወዲያው ወደ ጉምሩክ ጣቢያው እንዲገባ ይደረጋል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Revenues and Customs Authority



Addis Ababa, Ethiopia

3) ዲክላራሲዮን የተከፈተበት ጣቢያ የውጭ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ የሚገኝ ልዩነትን በሚደርሰው የፍተሻ ውጤት እና ይህንኑ በማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ በአስተዳደራዊ ወይም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት በፍርድ ቤት ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገዉ ቢኖርም በጎረቤት አገሮች ማስተባበሪያ ቅ/ጽ/ቤቶች በሚደረግ ፍተሻ ልዩነት ሲገኝ ዕቃዉ ወደ ሚላክበት ቦታ በመላክ የልዩነት ዉጤቱን የዉጭ ፍተሻ ለጠየቀው ቅ/ጽ/ቤት ያሳዉቃል፡፡

16. ስለማመልከቻ አቀራረብ

በዚህ መመሪያ አራት ላይ የተዘረዘሩት እቃዎች ላይ የውጪ ፍተሻ እንዲደረግ የሚጠይቅ ዲክላራሲዮን አቅራቢ ጥያቄውን ዕቃው ወደ አገር ከመግባቱ በፊት ወይም ከገባ በኂላ በፅሑፍ እና አግባብ ያላቸውን ሰነዶች በማያያዝ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

17. ማመልከቻን ስለመመርመር

1) አቤቱታ የቀረበለት የገቢ ወይም ወጪ ዕቃ ቡድን አስተባባሪ ማመልከቻውና አስፈላጊ ሰነዶች እንደቀረቡለት አቤቱታን መርምሮ ወዲያውኑ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው እንዲለቀቁ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

2) ሰነዶቹ ሲመረመሩ ወይም ዕቃዎቹ ሲፈተሹ በመመሪያው ክፍል አራት ስር ከተዘረዘሩት ዕቃዎች ወይም ባለመብቶች መካከል ያልሆኑ እንደሆነ እና በልዩ ሁኔታ በመመሪያው አንቀጽ 12 ንዑስ ቁጥር 3 በጉምሩክ ጉዳዮች ም/ሥራ/ አስኪያጅ ፈቃድ ያልተሰጣቸው እንደሆነ በመደበኛው ስነ-ስርዓት እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡

18. የውጪ ፍተሻ ስለመከልከል

ፈቃድ የሚሰጠው ቅ/ጽ/ቤት ተጨባጭ መረጃን ወይም ጥቆማን መሠረት በማድረግ፣ ወይም በልዩ ሁኔታ ለቀረቡ ጥያቄዎች አሳማኝ ምክንያት ያልቀረበ መሆኑን መሠረት በማድረግ የውጭ ፍተሻን ሊከለክል ይችላል፡፡

19. መረጃ ስለመያዝ

በዚህ መመሪያ መሰረት ፍተሻ ተደርጎ ልዩነት የተገኘባቸው ጉዳዮች በግብር ከፋዮች ስጋት ጥሮፋይል ዳታቤዝ (TPRDP) የመረጃ ስርዓት መሰረት መመዝገብ ይርባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

## ክፍል አምስት

## ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምባቸው ዕቃዎች

20. ዓይነት

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እቃዎች ወደ አገር ከገቡ በኋላ ወይም ሳይገቡ የዲክላራሲዮን አቅራቢ በሚያቀርበው ማመልከቻ መሰረት በባህሪያቸው ወይም በሚሰጡት አገልግሎት ምክንያት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት እንዲፈፀም ሊፈቀድ ይችላል፡፡

ሀ/ መድሐኒቶች፣

ለ/ በቀላሉ የሚቀጣጠሉ እቃዎች፣

ሐ/ ጨረር አመንጪ መሣሪያዎች፣

መ/ ዘር እና ችግኞች፣

ሠ/ በሕይወት ያሉ እንስሳት፣ ጫጩትና የመሳሰሉት፣

ረ/ ለምርመራና ለላብራቶሪ የሚውሉ ነፍሳት ወይም ዕጮች፣

ሰ/ ለወጪ እቃዎች ግብዓት የሚሆኑ እቃዎች፣

ሸ/ በመትነን አካባቢን የሚበክሉ ኬሚካሎች፣

ቀ/ ወቅታዊ የሆኑ መጽሔቶችና ጋዜጦች፣

በ/ ምግቦች፣ ፍራፍሬዎች፣

ተ/ ወጪ እቃዎች፣

ቸ/ በባለስልጣኑ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች እና የልዩ መብት ተጠቃሚዎች የሚያስወጧቸውና የሚያስገቧቸው እቃዎች ፣

ኀ/ ለአንድ ተቋም መደበኛ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ እና ከዕቃዎቹ ባህሪ አንጻር ለተጠቃሚው በአፋጣኝ መድረስ ያለባቸው እና ካልገቡም በሥራው ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ እቃዎችና መለዋወጫዎች፣

ነ/ በአዋጁ የተቀመጠው ስነ-ስርዓትና መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ እቃዎች

ኘ/ ሌሎች ባለሥልጣኑ በሚያስተላልፈው ሰርኩላር ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት እንዲፈጸምባቸው የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ወይም ዝርዝር የሚያሟሉ እቃዎች፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

## ስለማመልከቻ አቀራረብ

በዚህ አንቀጽ መሠረት ማመልከቻ የሚቀርበው፡-

1) በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (ሀ)-(ቸ) የተዘረዘሩትን እቃዎች በተመለከተ ማመልከቻው ሚቀርበው ለዕቃ አወጣጥ ቡድን ይሆናል፣
2) በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (ኀ)-(ኘ) የተዘረዘሩትን እቃዎች በተመለከተ ማመልከቻው የሚቀርበው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻፀም የስራ ሂደት ይሆናል፣
3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 ላይ የተዘረዘሩት እቃዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ከጉምሩክ ቁጥጥር እንዲለቀቁ የሚጠይቅ ዲክላራሲዮን አቅራቢ ጥያቄውን ዕቃው ወደ አገር ከመግባቱ በፊት ወይም ከገባ በኂላ በፅሑፍ እና አግባብ ያላቸውን ሰነዶች በማያያዝ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 22. ማመልከቻን ስለመመርመር

1) አቤቱታ የቀረበለት የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የስራ ሂደት እና የዕቃ አወጣጥ ቡድን ማመልከቻውና አስፈላጊ ሰነዶች እንደቀረቡለት አቤቱታን መርምሮ ወዲያውኑ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ተፈጽሞባቸው እንዲለቀቁ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡
2) ሰነዶቹ ሲመረመሩ ወይም ዕቃዎቹ ሲፈተሹ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 20 ስር ከተዘረዘሩት መካከል ያልሆኑ እንደሆነ በመደበኛው ስነ-ስርዓት እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡

## 23. ማመልከቻን ስላለመቀበል

ፈቃድ የሚሰጠው ቅ/ጽ/ቤት መረጃዎች ተሟልተው ያልቀረቡለት እንደሆነ ወይም በልዩ ሁኔታ ለቀረቡ ጥያቄዎች አሳማኝ ምክንያት ያልቀረበ መሆኑን መሠረት በማድረግ ማመልከቻውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 24. ስለተሻሩ መመሪያዎች

1) የዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 58/2003 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሰርኩላሮች እና ልማዳዊ አሠራሮች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሰረት እስከሚወሰን ድረስ ስለዚሁ የሚደነግጉት የመመሪያ ቁጥር 58/2003 ክፍል አምስት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡



Addis Ababa, Ethiopia

_የመሸጋገሪያ ድንጋጌ_

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን የቀረበባቸውና ተቀባይነት ያገኙ ዲክላራሲዮኖች በነበረው መመሪያ መሠረት ይስተናገዳሉ።

26. _መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ_

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ 12/09/ ቀን 2008

አብርሃም ንጉሴ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ተጠባባቂ ዋና ዳይሬክተር